# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
**Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)**

ጥቅምት 14 ቀን 2001 ዓ.ም

## በእስረኞች ላይ የሚደረገውን ስየል፣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ጥሰት ኢሕአፓ ያወግዛል

ከናይሮቢ ወደሞቃዲሾ በኃይል የተጋዙ እስረኞች ወደአዲስ አበባ ተወስደው በድብቅ እስር ቤቶች በወያኔ ወታደሮችና በአሜሪካኖች ስየል እንደተፈፀመባቸው አጋልጠዋል:: እስርቤቱና ምርመራው በአሜሪካኖች ቁጥጥር ሥር የሚካሄድ ይመስለኛል ብሏል ከተፈቱት እስረኞች አንዱ:: የተወሰኑ እስረኞች ተለቀው ኬኒያ የገቡ ቢሆንም ሌሎች 22 እስረኞች "የአፍሪካ ጓንታናሞ" ሊባል በሚችል እስር ቤት ውስጥ በኢትዮጵያ እንደሚገኙ ታውቋል::

ኢሕአፓ ጨቋኝ በሆነው የወያኔ አገዛዝ በእስረኞች ላይ እየተፈጸመ ያለውን ስየት እያወገዘ፣ ማንኛውም የውጭ ኃይል የሀገሪቱን ሉዓላዊነት በመጣስ እስርቤቶችን መቆጣጠርንና ስየት መፈጸምን አጥብቆ ይቃወማል:: አንዳንዶቹ እስረኞች ኬንያ ውስጥ ታስረውና ምርመራ ተካሂዶባቸው አሜሪካዊ በሆኑ ኤጀንቶች ወደ ሞቃዲሾ መወሰዳቸውን አስተማማኝ የሆኑ ሪፖርቶች ገልጸዋል:: ይህ ሪፖርት እንደሚያሳየው አብዛኞዎቹ እነዚህ እስረኞች ደግሞ ኬንያውያን በመሆናቸው የኪባኪን መንግሥት ተባባሪነት የሚያጎላ ሆኗል:: የበለጠ ማረጋገጫን የሚጋብዙ አንዳንድ ሪፖርቶች ደግሞ ጓንታናሞ መሰል እስርቤቶች በደቡብ ኢትዮጵያ በሁርሶ ወታደር ማሰልጠኛ እንደሚገኝ ጠቁመዋል:: የአሜሪካን ልዩ ወታደራዊ ኃይላትና ማሪኖች በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፍረው እንደሚገኙና በኬኒያ ወሰን አቅራቢያ በሚገኘው ብላቴን ወታደራዊ ማሰልጠኛ የወያኔን ኮማንዶዎች የሚያሰለጥኑ መሆናቸውም ግንዛቤን ሊያገኝ ይገባል::

ኢትዮጵያውያን ምንም ዓይነት የውጭ ኃይል ወታደራዊ የጦር ሰፈርና ወታደሮች በኢትዮጵያ ምድር መኖር እንደሌለባቸው ብሎም የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መከበር እንዳለበት በተደጋጋሚ መጠየቃቸው ይታወሳል:: ይህ በኢትዮጵያ ሕዝብ የቀረበ ጥሪ ግን በወያኔ የዝሆን ጆሮ ተሰጥቶት በተደጋጋሚ ሲጣስና በተጨባጭም ድንበር አልፎ ሶማሊያን መውረሩን፣ በሱማሌ ሕዝብ ላይም ምን ያህል የኑሮ ምስቅልቅልና መፈናቀል እንዳስከተለ የዓለም ሕዝብ ጭምር በግላጭ ያየው ጉዳይ ነው::

**በሕገወጥ መንገድ የታሰሩት እስረኞች በሙሉ**
**ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አሁኑኑ ይፈቱ!!!**
**የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት መጣሱ ይቁም!!**

**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**E-mail** ESPIC@aol.com

**Website:** http://www.EPRP.com

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France